# ሰው እንጂ ሕዝብ አላጣሽም

(ክፍል አንድ)

(ግጥም ከሂኖክ የሺጥላ)

በቁንጽል ፍቅር ያልተወጋሁ፣
ጽንፍ የፍቅር መናኜ፣
ፍቅር እንደ ኸረት የሙኸብኝ፣
የኢትዮጵያዊነት ምስለኔ፣
ረቂቅ የንጋት መዝሙር፣
ለቂቅ የብርሃን በር፣
አብ በአእዋፋት ልሳን፣
የሚከረከረው ክራር፣
ያጥብያ ኮከብ በዠርባቸው የሚመጠምጡት ጠፈር፣
መንኩሳት የሚማልሉት... የጣና ገዳም ቀመር ...
እህል ቆልተው፣
ቀርከሃን ለብዕር ቀርፀው፣
ፍቅር እየንከሩ፣
አንድነት እየመከሩ፣
በብራና ላይ የሙቱት፣
እመ ንቢያ ክትብት፣
እሱን ማወቅ ነው እጣዬ፤

ማወቅ ነው የኔ ፍላጎት፣
የጥቁር አፈሬን ጉልበት፣
ሲገፉት የሚሸሽ ሳይሆን፤ በሞት የሚጸና እውነት....

መሆን ነው...
በረጅም ዋሻ የሚያዝ፣
ሽንጡ ላይ የሚመረቅዝ፣
ፅልሙትን አልፎ የበራ፣
ባህር ከፍሎ ህዝብ የመራ....

መሆን ነው የኔ ፍላጎት፣
ለታሪኬ ሙክራብ መሞት...።
ከያዘሽ አሽክላ ለፊውስ፣
ግንባር እናቴ ቢቆረስ፣
ቅንጣት ታህል አይቆጨኝም፣
"ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም"
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም!

እምባሽን ከሚፀንፅል፣
ስቃይሽን ከሚደልል፣

መጥፌያሽንም በአንቀጽ፣
ከሚከትብ ከሚፈድል...
ሃዘንሽ ረብጣ ችሮት፣
እሱን ባንቺ ላይ አኑሮት፣
ለቀብርሽ ከሚማልል፣
ቃል ለምድር ለሰማይ፣
እኔስ ከሱ ጋ ላልታይ::

ገፅሽ በማዲያት ሲፈተን፣
እምቅ ጉልበትሽ ሲበተን፣
የወገብሽ ጥብቅ ሲላላ፣
ቅርስሽ በባዕድ ሲበላ...::

ድንበርሽ እየተገፋ፣
የክብርሽ ጠረን ሲጠፋ....::

መነኩሳቶችሽ ምስጋናን: ማክሌትሽን ሲመክኑ፣
ከገዳማቱ ተገፍተው: ባደባባይ ሲለምኑ፣
በዘር ማንነት ሲወሰን፣
ምደረ አዳሜ ክብርሽን ንፅህናሽን ሲወስብ፣
ብርሓንሽን ሳይጠግብ: ልጅሽ በብራ ሲረሽን...
ታሪክን ብቻ እያወሩ፣
ማ! ቢወልድ ማ! የዘር ግንድ፣
የንጉስ ደም እየጠሩ፣
ቅንጣት ታህልም ሳይጠሩ፣
ህሊናቸው ላይ ሸፍተው፣
ተደብቀው በሚኖሩ፣
በነሱ ቀንሽ አይመሽም፣
"ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም"
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም::
ዘመን ቢያልፍም፣
ከህደት መሰልጠን ሆኖ ዝባዝንኬውን ቢያጎርፍም፣
ለትግሉ ነው ህይወቴ......
እቴ አንቺ መርአቴ::

ሸማ የሸመንሽበት: የማይላላው ጥብቅ ክንድሽ፣
እንዝርትን ያሾረው እጅሽ...
ቀፎውን በማር የሞላው፣
አክሱም ፅዮንን ያቆመው፣
የሃን ከግርሽ ስር ያነፀው፣
ለክብርሽ ሳባን ያስነሳው፣
ሰ'ብ- አ ሠገልን ያነቃ፣
ማር በሊታውን በስምሽ መቅድስ እንዲያቆም ያበቃ...
ስንዱ ፍቃድሽ የታል?...
ውዴ ያንቺ ነውና.....

ምሽራው ዛሬም ለስምሽ ለህልውናሽ ይሞታል....።

ምድርሽ አደይን ሲቀባ...
ያሬድ ቅኔን አገልድሞ፣
በወረብ መቅደስ ሲገባ...
ህጣናቶቹ መስከሽ ላይ ቁግ እያስደነፉ፣
...የቡሄን ጅራፍ ሲገርፉ፣
አበባ በምድርሽ አይተው...
አበባ አየሁኝ ምስጋና...
እነሱም ቅኔን ሲዘርፉ....
የኖርሽው ዘመን ይመለስ...
ብርሃን ምድርሽን ይውረስ!

ህገሬው በሃገርኛ...
ኬር ይሁን ይባረክ ያሉት፣
ጠቢቦች ኮከብ እያዩ፣
ደርሰው ደጃፉን የሳሙት፣
አንቺ የክብር እመቤት....
መርአቱ የኔ ሙሽራ....
አንቀጽሽ ከደጅ ቆሞዋል፣
ፍቀጂው ብርሃን ያብራ።

ካንቺ መኻጠን ተጥሎ...
በ-ማእዶት፡ በምስጋና... ሰርቅ ማህሌትን ቆሞ...
ስጋውን ላንቺ በድሎ፡ ጥቁር አፈርሽን ቅሞ...
በማለዳ ይጠራሻል....
ሙሽራው ከልፍኝች ይግባ...
እቴ እሱ ይሻልሻል።

እናም ይህን እልሻለሁ....
አይኑን በጨው የታጠበ
ነጻ ወ'ጥቶ የጠበበ...
ከርስ ሆድ እቃው ተወጥሮ
የነብሱ ክር የረገበ...
ውጭ አካሉ ተሰድሮ
ግንዛቤው የነተበ...
ብልህነቱ የበላው፣
ታዛዥነቱ ያጎላው፣
ዛሬ ምድርሽ ላይ ቢነግስም....
ሰው እንጂ ህዝብ አላጣሽም፣
በሞትሽ ላይ እኔ አልሸሽም...።
እናም ይህን እልሻለሁ፣
ያንቺ ታርክሽ አይገሽብም፣
እንደስንቅ የገብስ ቆሎ....በዘር ሚጥሚጣ ቢታሽም፣
ሊያጠፉት እንጂ ሊያጣፍጡት

እንዳልሆን አይጠፋሽም...::

የስራታቸው ስርይቱ....
መሰልጠን ነው መሰሪነት....
ባሻገር ላይ መዶለቱ.....
እና ይህ የጉንዳን ባላባት...
ከማድንሽ ቢሰለፍ፣
ከደቡብ ከሰሜን ቢዘርፍ፣
ውስጥ ውስጡን እየተሳበ ... ከማንነትሽ ላይ ክብርን፣
መዐድንሽን ቢቀርፍ፣
ይህ የጨለማ ቀፈፋ፣
ህዝቡ በብሶት ሲገፋ፣
ከጉድጓድ ያኖረው ወጥቶ....
እሱ ጉድጓድ ውስጥ ይኖራል፣
ይህንን አንቺም ታውቅያለሽ ታሪክ ራሱን ይደግማል::
ይህንን አንቺም ታውቂያለሽ...

ይሄ የክልል ቁምስና፣
በትውፊትሽ ላይ ሙስናን፣
በህዝብሽ ላይ ሽርሙጥናን....
የሙጢኝ ብሎ ሲጠና፣
እያይሁ ዘመኔ ከሚያልፍ፣
ፍቃድሽ ይሁን አንቺ 'እቴ፣
ለክብርሽ ይለፍ ህይወቴ ....

ያርገኝ ለወጋግራ፣
ለድግርና ለሞፈር፣
ለትንሳኤሽ የምሰዋ...
ለታርክሽ የምገበር....

ትናንት እንኩዋ በመስመሬ በስንኜ ስዘክርሽ፣
ያጨበጨቡበት መዳፍ: ገና ሙቀቱ ሳይለቀው...
እነሱ ከኔ ተሽለው: ለዚህ ህይወቴ ተጨንቀው፣
"ምን ይሰራል ቦጠሊቃ እርፈህ ትምህርትህን ተማር"
የሚል የባንዳ በገና: ያውም "ባ'ለ እስራአንድ አውታር" ...
እንሱ ከበኩቱበት: ከፈተፈቱት ዘኬይቸው፣
ሊያውም ካውሮጳና አሜሪካ: በተቸጠረ ምሳቸው...
ይሄን የነገር እንግዴ ...
ደሞ እንዲደርሰው ለሆዴ ...
በሰለጠነ ልመና...
"ምክር" በተባለ ዘዴ ...
ሲያንቆረቁረው አደረ: እባኝ ተብየው ዘመዴ::

"ቤተሰብ መስርት" ምናምን :
ስንዱ እንዲህ .... ይለኛል ....

